# የወንድ ብልት ቀዶ ጥገና

## ከቀዶ ጥገና በኋላ እንክብካቤ

**ከቀዶ ጥገናው ወይም የሕክምና ሂደቱ በኋላ ልጅዎን እንዴት እንደሚንከባከቡ የሚረዱ ደረጃዎች**

### ልጄ ምን አይነት ቀዶ ጥገና ነበረው?

- ❑ ከብልት ጭንቅላት ጋር የተገናኘ ቆዳን ማስወገድ (lysis of penile adhesions)
- ❑ የሽንት ቱቦ መከፈት (meatotomy / meatoplasty)
- ❑ ሸለፈት ማስወገድ (ግርዛት)
- ❑ በቆዳ የተቀበረው ብልት መጠገን
- ❑ የታጠፈ ብልት ማስተካከል (የወንድ ብልት ማስተካከል)
- ❑ ወደታች የተጠመዘዘውን የወንድ ብልት ማስተካከል (chordee)
- ❑ በወንድ ብልት ላይ ያበጠውን ማስወገድ (excision)
- ❑ ሌላ ______________________________

### ልጄ መቼ ነው ወደ ቤት መሄድ የሚችለው?

አብዛኛዎቹ ልጆች ቀዶ ጥገናው በተደረገበት ቀን ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ። ልጅዎ ሌላ የጤና ችግር ካለበት በክሊኒኩ ማደር ሊያስፈልገው ይችላል።

### ከቀዶ ጥገና በኋላ ልጄን እንዴት መንከባከብ እንዳለብኝ የሚያብራሩ ቪዲዮዎችን የት ማየት እችላለሁ?

ከቀዶ ጥገና በኋላ ልጅዎን እንዴት እንደሚንከባከቡ ለማብራራት ቪዲዮዎችን አዘጋጅተናል። የእነዚህ ቪዲዮዎችን ርዕሶች በ YouTube ላይ መፈለግ ይችላሉ። በእድሜ ገደቦች ምክንያት የአካውንትዎ መለያ በመስጠት መግባት ይኖርብዎታል።

- "ከዩሮሎጂክ ቀዶ ጥገና በኋላ ልጅዎን እንዴት እንደሚንከባከቡ"
  youtube.com/watch?v=epLQn5D62wk
- "ከወንድ ብልት ቀዶ ጥገና በኋላ ልጅዎን እንዴት እንደሚንከባከቡ"
  youtube.com/watch?v=ppZeEKY848M

### ቀዶ ጥገና የተደረገበትን የሰውነት ክፍልን እንዴት መንከባከብ እችላለሁ?

- በቀዶ ጥገናው በተደረገበት ክፍል ላይ ትንሽ የደም መፍሰስ ማየት የተለመደ ነው። የደም መፍሰሱ እስኪቆም ድረስ ለ 5 ደቂቃ ያህል በአካባቢው ላይ ረጋ ያለ ትንሽ ግፊት ማድረግ ይችላሉ።
- በወንድ ብልት ላይ ቢጫ ፊልም ማየት ይችላሉ። ይህ የሚፈወስ ሲሆን የተለመደ ነገር ነው።
- ከቀዶ ጥገናው ቀን ጀምሮ ቀዶ ጥገና በተደረገበት የወንድ ብልት ላይ ፔትሮሊየም ጄሊ (ቫስሊን) ያድርጉበት። ብልቱ በሚድንበት ጊዜ ይከላከላል።
- በእያንዳንዱ ጊዜ ከመካከለኛ እስከ ብዛት ያለው ፔትሮሊየም ጄሊ ይጠቀሙ።
- ፔትሮሊየም ጄሊውን በጣትዎ ወይም ጥጥ በመጠቀም ይቅቡት።
  - O ዳይፐር ለሚጠቀሙ ህጻናት፡- ይህንን ለ 2 ሳምታት ዳይፐር በሚቀይሩበት በእያንዳንዱ ጊዜ ያድርጉት።
  - O ዳይፐር ለማይጠቀሙ ልጆች፡- ይህን በሚቀጥሉት 2 ሳምንታት በቀን 3-4 ጊዜ ያድርጉ



**የበለጠ ለማወቅ**

- ዩሮሎጂ
  206-987-2509
- የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ይጠይቁ።
- seattlechildrens.org

**ነጻ የአስተርጓሚ አገልግሎቶች**

- በሆስፒታል ውስጥ ነርስዎን ይጠይቁ።
- ከሆስፒታሉ ውጭ በነጻ የሚያገለግል የቤተሰብ አስተርጓሚ መስመርን፡ በስ.ቁ
  1-866-583-1527 ይደውሉ። የሚፈልጉትን ስም ወይም ኤክስተንሽን ለአስተርጓሚው ያስታውቁ።

Seattle Children's®
HOSPITAL • RESEARCH • FOUNDATION

## ልጄ መቼ መታጠብ እና መዋኘት ይችላል?



ለልጅዎ እንክብካቤ ከዚህ በታች ባለው የቼክ ☑ ምክሮችን ይከተሉ።

- ❑ በቁስሉ ላይ የሰገራ ቆሻሻ ካለ፡ ቁስሉን ለማጠብ ልጅዎን ለአጭር ጊዜ በመታጠቢያ ገንዳ ውስጥ በማስገባት ማጠብ ይችላሉ። ይህ ከተከሰተ መሸፈኛ ፋሻውን ማውጣት አያስፈልግዎትም። በፋሻ ላይ የቆሻሻ እድፍ ሊጠበቅ ይችላል። መሸፈኛውን ማውለቅ አያስፈልግም።
- ❑ የቀዶ ጥገና ሀኪምዎ ካልነገረዎት በስተቀር ልጅዎ ገላውን መታጠብ እና መዋኘት ይችላል።
- ❑ የቀዶ ጥገና ሃኪማቸው ሻወር እና መታጠቢያዎች ደህና መሆናቸውን እስኪነግሩዎት ድረስ ልጅዎ በስፖንጅ በመወልወል ገላውን ማጽዳት ይችላል።
- ❑ ልጅዎ ከ 2 ቀናት በኋላ ሻወር መውሰድ ወይም በመታጠብያ ገንዳ ውስጥ መታጠብ ይችላል። ልጅዎ ከ 2 ሳምንት በኋላ መዋኘት ይችላል።

## የመሸፈኛ ፋሻውን እንዴት መንከባከብ እንችላለሁ?

ለልጅዎ እንክብካቤ ከዚህ በታች ባለው የቼክ ☑ ምክሮችን ይከተሉ።

ልጅዎ ከ 2 የፋሻ (መሸፈኛ) ዓይነቶች 1 አለው

- ❑ **ስስ እና ግልጽ መሸፈኛ፡-** ይህ ከቀዶ ጥገናው በኋላ ከ 2 እስከ 14 ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ በራሱ ይወድቃል። ይህንን ማስወገድ አያስፈልግዎትም።
- ❑ **ነጭ መሸፈኛ፡-** ይህንን ቀዶ ጥገና ከተደረገ ከ 2 ቀናት በኋላ በቤት ውስጥ ያስወግዱ። መሸፈኛው ከተጠበቀበት ጊዜ ቀደም ብሎ ከወደቀ፡ አይተኩት።

## መሸፈኛ ፋሻውን እንዴት አወጣዋለሁ?

- ልጅዎን ለ 10 ደቂቃ ያህል በሞቀ የገንዳ መታጠብያ ውኃ ውስጥ እንዲቀመጥ ያድርጉ። ይህ ፋሻውን ለማውጣት እና ለማስወገድ ቀላል ያደርገዋል። ፋሻው ለማውጣት ቀላል ካልሆነ፡ ልጅዎን በመታጠቢያው ገንዳ ውስጥ እንደገና ሌላ ከ10 እስከ 20 ደቂቃዎች እንዲቀመጥ ያድርጉት።
- ፋሻው አሁንም በቀላሉ የማይወጣ ከሆነ ወይም የተጣበቀ የሚመስል ከሆነ፡ 1 ኩባያ ዘይት (የቆሎ፣ የአትክልት፣ የወይራ ወይም የህጻን ዘይት) በወንድ ብልት ላይ ይቅቡት። ይህ ለ 20 ደቂቃዎች እንዲቆይ ያድርጉ እና ከዚያም ፋሻው ያስወግዱ።
- ፋሻው አሁንም የማይወጣ ከሆነ ለተጨማሪ ምክሮች ወደ ዩሮሎጂ ክሊኒክ ይደውሉ።

## ልጄ ምን ያህል እንቅስቃሴ ማድረግ ይችላል?





ለልጅዎ እንክብካቤ ከዚህ በታች ባለው የቼክ ☑ ምክሮችን ይከተሉ።

- ❑ የተለመደው እንቅስቃሴ
- ❑ ልጅዎ በእግሮቹ መካከል ያለውን ግፊት የሚጨምሩትን ማንኛውንም አይነት እንቅስቃሴዎችን ለ 2 ሳምንታት ያህል አያድርጉ። ይህ የሚያጠቃልለው:-
  - ልጅዎን በወገብዎ ላይ መሸከም
  - ልጅዎን በጉልበቶዎ ላይ አድርገው መወዛወዝ
  - ሕጻኑን የሚሸከሙበትን መሳሪያዎችን መጠቀም
  - መታጠቂያ ያላቸው ባውንሰር አሻንጉሊቶችን መጠቀም
  - ብስክሌቶች፣ ባለሶስት እግር ሳይክል ወይም የሚነዱ አሻንጉሊቶች
  - **የመኪና መቀመጫዎችን እና ወንበሮችን (highchairs) መጠቀም ምንም ችግር የለውም።**
- ❑ ለ 2 ሳምንታት ያህል አድካሚ የሆኑ ጨዋታዎች፣ አቀበት መውጣት፣ ንኪኪ ያለበት ስፖርት፣ እና በጂም ክፍሎች እንዳይሳተፉ። እንደ መመሪያ ልጅዎ በደምብ እስኪድን ድረስ በሁለቱንም እግሮች መሬት ላይ እንዲራመድ ያድርጉ።
- ❑ ልጅዎ በሐኪም የታዘዙ የህመም ማስታገሻዎች ወይም ብዙ ጊዜ በቀን የሚወሰዱ ከፋርማሲ የሚገዙ የህመም ማስታገሻዎች ከአሁን በኋላ የማይፈልግ ከሆነ ወደ የህጻናት መዋያ ወይም ትምህርት ቤት ሊመለስ ይችላል። የልጅዎ ትምህርት ቤት በልጅዎ ብልት ላይ ፔትሮሊየም ጄሊ ማድረግ የማይችገር መሆኑን ያረጋግጡ፤ ካልሆነ ግን ልጅዎ ይህንን በራሱ ማድረግ እንደሚያስፈልገው ያስታውሱ።

## ልጄ ህመም ይኖረዋል?

- ከቀዶ ጥገና በኋላ፡ ልጅዎ በወንድ ብልት ላይ ህመም ሊሰማው ይችላል። ህመምን በተቻለ መጠን ሙሉ በሙሉ ለማስታገስ ከእርስዎ እና ከልጅዎ ጋር በመተባበር እንሰራለን። ከማንም በላይ እርስዎ ልጅዎን በደንብ ያውቁታል። በልጅዎ ማገገም ላይ አስፈላጊውን ተሳትፎ እንዲያደርጉ እናበረታታዎታለን። የልጅዎ ህመም ደረጃ ምንም ይሁን ምን፡ ሕመሙን ይረዱና ወዲያውኑ ምላሽ ይስጡት።
- ውጤታማ የሆነ የህመም መቆጣጠሪያ ልጅዎ ጥሩ ስሜት እንዲሰማው እና በፍጥነት እንዲድን ይረዳል። Acetaminophen (Tylenol) እና ibuprofen (Advil ወይም Motrin) ህመምን ለማከም የተለመዱ መድሃኒቶች ናቸው። በእድሜ ትልልቅ የሆኑ ልጆች የኦክሲኮዶን (oxycodone) መድሀኒት እንዲወስዱ ሐኪሙ ሊያዝዝ ይችላል። ማንኛውንም አይነት መድሃኒት ለልጅዎ ከመስጠትዎ በፊት የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎን ያነጋግሩ።
- አብዛኛውን ጊዜ ለአብዛኞቹ ልጆች ከመጀመሪያው ቀን በኋላ፡ ጊዜ እያለፈ ሲሄድ ህመሙ የተሻለ ይሆናል። የህመም መቆጣጠርያ መድሃኒት ከመስጠትዎ በተጨማሪ ልጅዎን በሙዚቃ፣ በጨዋታ፣ በቲቪ ወይም በቪዲዮ በማዘናጋት እንዲቋቋም መርዳት ይችላሉ።
- ስለ ህመም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፡ "ጽኑ እና አጣዳፊ ህመም" የሚለውን ጽሑፋችን ያንብቡ። seattlechildrens.org/pdf/PE503AM.pdf

## ጥቅም ላይ ያልዋለ መድሃኒትን እንዴት መጣል አለብኝ?

የቤተሰብዎን ደህንነት ለመጠበቅ መድሃኒቶችን በተቆለፈ ካቢኔት ውስጥ ወይም ሌሎች በቀላሉ ሊደርሱባቸው በማይችሉበት ቦታ ውስጥ ያስቀምጡ። ልጅዎ ከቀዶ ጥገናው ካገገመ በኋላ ያልተጠቀሙበት መድሀኒቶችን በሙሉ ያስወግዱ።

ሆን ተብሎ ወይም ሳያውቁ በድንገት የተረፈውን የህመም ማስታገሻ ወይም ሌሎች መድሃኒቶችን መውሰድ በጣም አደገኛ ሊሆን ይችላል። ጥቅም ላይ ያልዋሉ የኦፒዮይድ መድኃኒቶችን በአስተማማኝ ሁኔታ ስለማስወገድ የበለጠ መረጃ ለማግኘት "የኦፒዮይድ መድኃኒቶችን ደህንነቱ የተጠበቀ አጠቃቀም እና አወጋገድ" seattlechildrens.org/pdf/PE3140.pdf የሚለውን ጽሑፋችን ያንብቡ፡ ወይም በአጠገብዎ የመመለሻ ቦታ ለማግኘት በ takebackyourmeds.org ይጎብኙ።

## መቼ ነው መደወል ያለብኝ?

ከሰኞ እስከ አርብ፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካልዎት ለዩሮሎጂ ክሊኒክ በስ.ቁ 206-987-2509 ይደውሉ። ለአስቸኳይ ያልሆኑ ጥያቄዎች የ MyChart መልዕክቶችን ይላኩ።

ምሽቶች፣ ቅዳሜና እሁዶች እንዲሁም በዓላት፡ በስ.ቁ 206-987-2000 ይደውሉ እና ተረኛው የዩሮሎጂ ሐኪምን በስልክ በማነጋገር ቀጥሎ የተዘረዘሩትን አስቸኳይ ስጋቶችን በተመለከተ ይጠይቁ፡-

- ከ 101.5°F (38.6° C) በላይ የሆነ ትኩሳት
- ወደ ጨጓራ አካባቢ የሚዘረጋ መቅላት እና እብጠት
- ለ 5 ደቂቃዎች ግፊት ከተጠቀሙ በኋላ ለማስቆም ያልተቻለ የደም መፍሰስ
- ልጅዎ በታዘዘው መድሃኒት ሊቆጣጠረው የማይችል ህመም ካለው
- ከቀዶ ጥገናው በኋላ ለ 8 ሰአታት ያህል መሽናት ካልቻለ
- ማቅለሽለሽ (ማስመለስ)

Seattle Children's መስማት ለተሳናቸው፣ የመስማት ችግር ላለባቸው ወይም ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ውጭ ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ ህመምተኞች፣ ለቤተሰብ አባላት፣ እና ለህጋዊ ተወካዮች የአስተርጓሚ አገልግሎቶችን በነጻ ይሰጣል። የ Seattle Children በተጠየቁ ጊዜ ይህንን መረጃ እንደ አማራጭ በሌላ ቅርጸቶች ያቀርባል። በ 206-987-2201 ለ Family Resource Center ይደውሉ። ይህ የሚታደል ጽሑፍ በ Seattle Children ክሊኒካዊ ሠራተኞች ተገምግሟል። ቢሆንም፡ የልጅዎ ፍላጎቶች ከሌሎች ልጆች ፍላጎት የተለዩ ናቸው። በዚህ መረጃ ላይ እርምጃ ከመውሰድዎ ወይም ከመተማመንዎ በፊት፡ እባክዎ ከልጅዎ የጤና አጠባበቅ አቅራቢ ጋር ይነጋገሩ።

8/22
PE2940AM

© 2022 Seattle Children's፡ ሲያትል፡ ዋሽንግተን። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

# Penile Surgery

## Care After Surgery

**Steps for caring for your child after their surgery or procedure**

### What type of surgery did my child have?

- ❑ Removal of skin connected to head of penis (lysis of penile adhesions)
- ❑ Opening of the urethra (meatotomy / meatoplasty)
- ❑ Removal of foreskin (circumcision)
- ❑ Buried penis repair
- ❑ Correction of bent penis (penile angulation)
- ❑ Correction of downward curve in penis (chordee)
- ❑ Penile cyst removal (excision)
- ❑ Other ____________________________________________

### When can my child go home?

Most children go home the day of surgery. If your child has another medical condition, they may need to stay overnight.

### Where can I watch videos that explain how to care for my child after surgery?

We created videos to explain how to care for your child after surgery. You can search for these titles on YouTube. You may need to login due to age restrictions.

- "How to Care for Your Child After Urologic Surgery"
  **youtube.com/watch?v=epLQn5D62wk**
- "How to Care for Your Child After Penile Surgery"
  **youtube.com/watch?v=ppZeEKY848M**

### How do I care for the surgery site?

- It is normal to see a small amount of bleeding at the surgical site. You can apply gentle pressure to the area until the bleeding stops for up to 5 minutes.
- You can expect a yellow film on the penis. This is normal as it heals.
- Starting the day of surgery, put petroleum jelly (Vaseline) over the surgical site on the penis. It will keep the penis protected while it heals.
- Use a moderate to large amount of petroleum jelly each time.
- Put the petroleum jelly on with your finger or a cotton swab.
  - For children in diapers: do this at every diaper change for the next 2 weeks
  - For children not in diapers: do this 3-4 times a day for the next 2 weeks



**To Learn More**

- Urology
  206-987-2509
- Ask your child's healthcare provider
- **seattlechildrens.org**

**Free Interpreter Services**

- In the hospital, ask your nurse.
- From outside the hospital, call the toll-free Family Interpreting Line, 1-866-583-1527. Tell the interpreter the name or extension you need.

Seattle Children's®
HOSPITAL • RESEARCH • FOUNDATION

## When can my child take a bath and swim?




Follow the tips with a check ☑ below for your child.

- ☐ You can briefly place your child in the bathtub to rinse off the wound if poop gets onto it. You do not need to remove the dressing if this happens. Staining on the bandage can be expected. There is no need to take the dressing off.
- ☐ Your child can take a shower or bath and go swimming unless your surgeon tells you not to.
- ☐ Your child may have a sponge-bath only until their surgeon tells you showers and baths are ok.
- ☐ Your child may shower or take a bath after 2 days. Your child may swim after 2 weeks.

## How do I care for the dressing?

Follow the tips with a check ☑ below for your child.

Your child has 1 of 2 types of dressing:

- ☐ **Clear dressing**: this will fall off on its own some time from 2 to 14 days after surgery. You do not need to remove this.
- ☐ **White dressing**: remove this 2 days after surgery at home. If the dressing falls off early, do not replace it.

## How do I remove the white dressing?

- Have your child sit in a warm bath or shower for about 10 minutes. This will loosen the dressing to make it easier to remove. If the bandage is not loosening, have your child sit in the bath for 10 to 20 more minutes.
- If the dressing is still not coming off easily or is stuck, put 1 cup of oil (corn, vegetable, olive or baby oil) on the penis. Allow this to soak in for 20 minutes and then remove the dressing.
- If the dressing is still not coming off, call the urology office for more tips.

## How much activity can my child do?





Follow the tips with a check ☑ below for your child.

- ☐ Normal activity
- ☐ Avoid any straddle activities with your child that increase pressure between their legs for 2 weeks. This includes:
  - Holding your child on your hip
  - Bouncing your child on your knee
  - Baby-wearing devices
  - Bouncer toys that have a harness
  - Bicycles, tricycles or ride on toys
  - **It is ok to use car seats and highchairs.**
- ☐ Avoid rough play, climbing, contact sports and gym class for 2 weeks. Have your child keep both feet on the ground as a guideline until they are done healing.
- ☐ Your child may return to daycare or school when they no longer need prescription pain medicine or frequent daytime over-the-counter pain medications. Check if your child's school is comfortable with putting the petroleum jelly on your child's penis or your child will need to be able to do this on their own.

## Will my child have pain?

- After surgery, your child may feel pain on the penis. We partner with you and your child to relieve pain as completely as possible. No matter the level of your child's pain, believe they are hurting and respond right away.
- Effective pain control will help your child feel better and heal faster. Acetaminophen (Tylenol), ibuprofen (Advil or Motrin) or both are common medicines to treat pain. Older children may receive oxycodone. Check with your healthcare provider first before giving any type of medicine to your child.
- The pain will get better as time passes, usually after the first day for most children. In addition to medicine, you can also help your child cope by distracting them with music, games, TV or videos.
- For more information, read our handout "Acute Pain". **seattlechildrens.org/pdf/PE503.pdf**

## How do I dispose of unused medication?

To keep your family safe, store medicines inside a locked cabinet or location where others cannot easily get to them. Once your child has recovered from surgery, dispose of all unused prescription medicines.

Taking leftover pain or other medicines on purpose or by accident, can be very dangerous. For more information about safe disposal of unused opioid medications, read our handout "Safe Use and Disposal of Opioid Medicines" at **seattlechildrens.org/pdf/PE3140.pdf** or visit **takebackyourmeds.org** to find a take back place near you.

## When do I call?

Monday to Friday, call the Urology clinic at **206-987-2509** for questions or any of the concerns listed below. Send MyChart messages for non-urgent questions.

Nights, weekends and holidays, call **206-987-2000** and ask for the Urology resident on call for urgent concerns from the following list:

- Fever higher than 101.5° F (38.6° C)
- Redness and swelling that spreads up into the stomach area
- Bleeding that cannot be stopped after 5 minutes of applied pressure
- Your child has pain not controlled by the medicine prescribed
- Cannot pee for a span of 8 hours after surgery
- Throwing up (vomiting)

Seattle Children's offers free interpreter services for patients, family members and legal representatives who are deaf or hard of hearing or speak a language other than English. Seattle Children's will make this information available in alternate formats upon request. Call the Family Resource Center at 206-987-2201. This handout has been reviewed by clinical staff at Seattle Children's. However, your needs are unique. Before you act or rely upon this information, please talk with your healthcare provider.

© 2022 Seattle Children's, Seattle, Washington. All rights reserved.

8/22
PE2940